# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል
# 20 ኛ ሳምንት
# አመስጋኙ ሰው

**ዓላማ**

- ስለ ጌታችን በፈጸማቸው ተዓምራት መሠረት መማር፡፡

**ምንባብ**

- ሉቃስ 17፡11-17

**ትምህርቱ**

- አንድ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አንዲት ትንሽ መንደር ሲገባ፣ አሥር ለምጻሞች ከሩቅ ተገናኙት፡፡
- ልጆች ለምጽ ምን እንዲሆን ታውቃላችሁ? …… የቆዳ በሽታ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ የኃጢአት ምልክት ተደርጎ ይቆጠር ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ለምጽ ያለባቸው ከማኅበረሰቡ ይገለሉ ነበር፡፡ ከሕዝቡ እንዲቀላቀሉም አይፈቀድላቸውም ነበር፡፡ ለዚህም ነው ከጌታችን ርቀው የቆሙት፡፡
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያዩትም እየጨኹ ***"አቤቱ ማረን"*** አሉት፡፡ መድኃኒታችንም ***"ሂዱ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ"*** አላቸው፡፡
- ሄደው ራሳቸውን ለካህናት ሲያሳዩ/ተናዘው ሲመስሉት ከለምጻቸው ዳኑ፡፡ ቆንጆ ቆዳም ሆነላቸው፡፡ ከእነርሱ አንዱ የተደረገለትን አይቶ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን እያመሰገነና እያከበረ ተመለሰ፡፡ በጌታችን እግር ፊት በግንባሩ ወድቆም አመሰገነው፡፡
- ጌታችንም ***አሥሩ አልዳኑምን? ዘጠኙ ወዴት አሉ? ከአንዱ በስተቀር ሊያመሠግን አልመጣምና ተነሣና ሂድ እምነትህ አድኖሃል*** አለው፡፡

**ጥያቄ**

1. ራስን ለካህን ማሳየት ምን ማለት ነው?
2. ለምጻሞቹ ጌታን ሲያዩት ምን አሉ?
3. ከዳኑት ለምሥጋና ስንት ሰው ተመለሰ?
4. አመስጋኙን ጌታችን ምን አለው?
5. ከዚህ ምን ተማራችሁ? ለመምህርና ለቤተሰብ አስረዱ፡፡

**መዝሙር**

ተናገሩ ድንቅ ሥራውን መስክሩ
ተዓምሩን ለዓለም ንገሩ፡፡ ድንቅ ሥራውን መስክሩ

## ጾም

**ዓላማ**

- ስለ ጾም ጥቂት መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**

- "ጾምን ቀድሱ" ኢዩ 2÷15

**ምንባብ**

- ማቴ.4÷1-11

**መግቢያ**

- ልጆች ከፊታችን ሰኞ ጀምሮ ዐቢይ ጾም እንደሚገባ ታውቃላችሁ? ጾም ምን ? እንደሆነና ለምን ?እንደሚጾም እንማራለን፡፡

**ትምህርቱ**

- ቤተክርስቲያን በዐብይ ጾም ምን ይደረጋል?
  - ✓ ይቀደሳል፣ ይጸለያል፣ ይሰገዳል፣ ይዜማል፡፡
- ጾም ምንድነው?
  - ✓ ከምግብና መጠጥ ለተወሰነ ሰዓታት እንዲሁም ከፍስክ ምግቦች በጾም ወቅቶች መከልከል ነው፡፡
- ለምን ይጾማል?
  - ✓ በረከት ለማግኘትና ክፉ ነገሮችን ለማሸነፍ፡፡
- ጌታችን እንዴት ጾመ?
  - ✓ 40 ቀንና 40 ሌሊት ሳይበላና ሳይጠጣ
- ጌታችን የት ቦታ ጾመ?
  - ✓ ቆሮንጦስ በተባለ በረሐ፡፡
- ጌታችን ለምን ጾመ?
  - ✓ መጾም እንዳለብን ሊያስተምረንና ዲያብሎስን ለማሸነፍ፡፡
- በጾም ምን ምን ይደረጋል?
  - ✓ ይቀደሳል፣ ይጸለያል፣ ይሰገዳል፣ የፍስክ አይበላም፣ ቅዳሴ ማስቀደስ ፣ መቁረብ ወዘተ….
- በቤተክርስቲያን ስንት አጽዋማት አሉ?
  - ✓ ሰባት
- በስም ጥቀሱዋቸው?
  - ✓ ዐብይ ጾም፣ ጾመ ነነዌ፣ ጾመ ነቢያት፣ ጾመ ሐዋርያት፣ ጾመ ፍልሰታ፣ጾመ ድኅነት/ረቡዕና አርብ/ እና ገሀድ ናቸው፡፡
- በስንት ዓመት \ዕድሜ\ መጾም ይጀመራል?
  - ✓ በ12 ዓመት
- መጾም ያልጀመሩ ሕፃናት በጾም ምን ያደርጋሉ?
  - ✓ ከቤተሰብ ጋር ቤተክስቲያን ሄደው ይጸልያሉ፣ ቅዳሴ በፀጥታ ይሰማሉ፣ ይቆርባሉም

**ተግባር**

1. ቤተሰብ ሲጸልይና ሲጾም በቤተክርስቲያንም መረበሽ አይገባም፡፡
2. በእሁድና በበዓላት ቀናት ከቤተሰብ ጋር ሂዱና ቁረቡ፡፡
3. ራሳችሁን ቤተሰባችሁንና ሀገራችሁን እግዚአብሔር እንዲባርክላችሁ በጸሎት ንገሩት፡፡

**ይቆየን፡፡**